## ‘ኢትዮጵያ -- ዛሬና ነገ’
## በነሐሴ 2005 ዓ/ም በአልፋ አታሚዎች የታተመ
## የፕሮፌሰር አሰፋ እንደሻዉ መጽሐፍ ግምገማ
## በዶ/ር በቀለ ገሠሠ

***መንደርደሪያ፤***

ፕሮፌሰር አሰፋ እንደሻዉ በጄነራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባልደረባዬ የነበሩ። እርሳቸዉ 12ኛ ክፍል ሳሉ ነበር እኔ 9ኛ ክፍል የገባሁት። በትምህርት ችሎታቸዉና በጸባያቸዉ የላቁ ስለነበሩ የማጥኛ ልዩ ክፍል ሁሉ በግላቸዉ ተሰጥቷቸዋል። እኔ በትርፍ ጊዜዬ የቅርጫት ኳስ ጨዋት አዘወትር ነበር። እርሳቸዉም እንደዚሁ በየ ግማሽ ሰዓት ከማጥኛ ክፍላቸዉ እየመጡ ይቀላቀሉንና ትንሽ ዱብ ዱብ ብለዉ ይመለሱ ነበር። በዚህ መልክ ሰዉነታቸዉንና አእምሯቸዉን እያደሱ በማጥናትና እግዚአብሔር በሰጣቸዉ ልዩ ጭንቅላት በማትሪክ ፈተና ላይ 11 ፈተናዎች ተቀምጠዉ በሁሉም የላቀ ዉጤት (A A A ....) በማለፍ ብቸኛ ሪኮርድ የጨበጡ ምሁር በመሆናቸዉ በሁሉም ዘንድ ልዩ ከበሬታ ያተረፉ ድንቅና ብርቅዬ ዜጋ ናቸዉ። ከዚያም በኋላ ለረዥም ዓመታት በደርግ ወህኒ ቤት ተሰቃይተዉ ወጥተዉ ወደ ትምህርታቸዉ በመመለስ በህግ ሙያ እስከፕሮፌሰርነት ማዕረግ የደረሱ ታላቅ ምሁር ናቸዉ።

በነዚያ ዉጤቶቻቸዉ ሳደንቃቸዉ የኖርኩ ሰዉዬ ዛሬ ደግሞ እላይ የተጠቀሰዉ አዲስ መጽሐፋቸዉ በእጄ ገባ። እጅግ በጣም የሚገርም ነዉ። መጽሐፉን የደረሱት በሩቅ ሆነዉ አይደለም። ወደ እናት አገራቸዉ ተመልሰዉ እያንዳንዱን የአገሪቱ ክፍል ደከመኝ ታከተኝ ሳይሉ ሁሉንም ተዘዋዉረዉ በመመልከት፤ አያሌ ሰዎችን በመጠየቅ፤ ያለፉትን ታሪኮች በመመርመርና በማገናዘብ የተዘጋጀ የጽሑፍ መረዣ ነዉ። ያን ሁሉ ቦታ ባላዳርስም እኔም ብዙዎቹን ቦታዎች ለማጥናት  ዞሬ የተመለከትኳቸዉ ስለሆነ ጽሑፉ እጅግ በጣም አርክቶኛል።

መጽሐፉ የማይዳስሰዉ አንገብጋቢ ቦታ አልቀረም። ስለፖሊቲካዉና ማህበራዊ ችግሮች፤ ስለቋንቋና ባህል፤ ስለፍልስፍናና ኪነት፤ስለስፖርትና መዝናኛዎች፤ ስለትምህርት ዘዴዎች፤ ዓላማዎችና ችግሮች፤ ስለፊልሞች፤ ወዘተ ብዙ ያትታል።

እጅግ ብዙ ትምህርት የሚገኝበት ስለሆነ ሁሉም ዜጋ መጽሐፉን ፈልጎ እንዲያነበዉ ላሳስብ እወዳለሁ።
a_endeshaw@yahoo.co.uk በሚለዉ ኢ-ሜይል አድራሻ ደራሲዉን ማግኘት ትችላላችሁ።

## ክፍል 1. “ ኢትዮጵያን እንዳየኋት“

የመጽሐፉ አንደኛዉ ክፍል ደራሲዉ የተለያዩትን የኢትዮጵያ ክፍሎች በሰፊዉ ጎብኝተዉ የተመለከቷቸዉን ሃቆች ይዘረዝራል፤ ከደሴ፤ ቦረና፤  ወልዲያ፤ ላሊበላ፤ ጎንደር፤ መቅደላ፤ ሰላሌ፤ የአባይ ሸለቆ፤ ባህርዳር፤ ደጀን፤ ደብረ ማርቆስ፤ ጅማ፤ አጋሮ፤ በደሌ፤ መቱ፤ ጎሬ፤ የዲዴሳ ሸለቆ፤ አርጆ፤ ነቀምት፤ ጉደር፤ አምቦ፤ መቀሌ፤ አክሱም፤ ሽሬ፤ ቡታጂራ፤ ሆሳዕና፤ ወላይታ ሶዶ፤ አርባ ምንጭ፤ ኮንሶ፤ ጂንካ፤ቱርሚ፤ያቤሎ፤ ላላታ ወንዶ፤ አንኮበር፤ መተሃራ፤ አዋሽ፤ ባሌ ጎባ፤ አሰላ፤ ሮቤ እስከ ላላባና ዱራሜ ድረስ።

ይሄን ክፍል ስመለከዉ አንጀቱን በላዉ፤ የማያቋርጥ እንባዬን አረገፈዉ።

- ስለጎጃምና አርሲ ቢኬድ ቢኬድ የማያልቅ የተንጣለለና የተዘረጋ ሰፊ ምድርና አዉላላ ሜዳ እየተመለከተ ጎጃምና አርሲን የሚያክሉ ምድራት ይዛ እንዴት ኢትዮጵያ ትራባለች? እያለ ይጨነቃል፤
- በጥንቱ ዘመናት አገራችን ታላላቅ ክንዋኔዎችን ፈጽማለች፤ ‘ምን ብናጠፋ ነዉ ከድሮዉ ታላቅ ክንዋኔዎች ወደዚህ መናኛ የህይወትና የአሰራር ዝቅጠቶች ዉስጥ የገባነዉ? ብሎ ይጠይቃል። እንደምሳሌ አድርጎ የነላሊበላን ገዳማት ይጠቅሳል። ጎንደር የታሪክ

ማህደርና የ44 ታቦቶች መናኼሪያ ሆና ሳለች ታሪካዊ ግንቦች ተንከባካቢ በማጣታቸው ምክንያት እየተደረመሱ፣ እየወላለቁና እየፈራረሱ መገኘታቸው እጅግ የሚያበግን መሆኑን ያሳያል።

- የኢሉ አባቦር ጥቀጥቅ ያለ ደን፣ ልምላሜና ቡና የሞላበት ሆኖ ሳለ ወደፊት ሳይራመድ ቆሞ ስለመቅረቱ፣
- በደቡቡ ክፍል የሙዝ፣ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ወዘተ ክምር የበዛበት ቢሆንም የሚያነሳቸው የጭነት መኪና እንኳን አለመኖሩ የሚያስተዛዝብ ስለመሆኑ፣
- ወዘተ፣

የዕድገት ተመራማሪ እንደመሆኔ መጠን እኔንም እጅግ የምያውኩኝ ጥያቄዎች ናቸው። ለሌሎች አገሮች የምትተርፍ የዳቦ ቅርጫት የነበረች አገራችን የድሆች አገር ሆና መቅረቷ ለሁላችንም የሞት ሞት ነው።

ባለፉት 50 ዓመታት አገራችን ብዙ የሣይንሥና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ሰጥታናለች። በተማርናቸው ትምህርቶችና በቀሰምናቸው ረዥም የሥራ ልምዶች በተለያዩ ዘርፎች ጎን ለጎን በመሰለፍ አገራችንን ማሳደግ እንችል ነበር፣

- በአፈርና በአካባቢ ጥበቃ፣
- በገጠር ገበሬወዎች ሁለገብ እርሻ
- በዘመናዊና ሰፋፊ እርሻዎች ዝርጋታ
- በፍራፍሬዎች ምርት
- በመስኖ አጠቃቀም
- በከብት እርባታ
- በጥቃቅን ቴክኖሎጂዎች ዕድገት
- በሰው፣ በሰብልና በከብት ጤና አጠባበቅ
- በሁሉም በሁሉም ዘርፍ።

ነገር ግን ለዚህ አልታደልንም። የተማረ ሰው የሚጠላባቸው ሥርዓቶች ተፈራረቁብን። "የዐባይን ልጅ ውሃ ጠማው"። ያገሩን ሕዝብ አደራጅቶ የሚያስፈልገውን ቴክንካዊና ቁሳቁሳዊ ድጋፎች በመስጠት ለዕድገትና ብልፅግና እንደማድረስ ያካባቢውን ሕእብ በማፈናቀል ስንት መቶ ሺህ ሄክታሮችን ለፓኪስታኖች፣ ለህንዶች፣ ለቻይናዎች፣ ወዘተ መስጠት የተለመደበት ሥርዓት ውስጥ ገባን። ከብቶቻችን እየተለቀሙ ወገኖቻችንን ለሚደበድቡ፣ ለሚገርፉ፣ ለሚያሰቃዩና ለሚገድሉ ዐረቦች ማቅረብ ቀለለ።

ተንከባካቢ መንግሥት ቢኖር አሁንም እነዚህን ችግሮች በሙሉ ቀርፈን ወደ አገራችንን ለዕድገት፣ ለብልፅግናና ለኩራት ልናበቃ የሚያስችል በቂ ችሎታና ሰፊ ዕድሎች እንዳሉን አንጠራጠር። እንደነህንድና ቻይና የመሳሰሉት አገሮች የተጠቀሙባቸውን የዕድገት ስልቶች ማጤን ይገባል። ከእኛ የተሻለ ለም መሬትና ብርቱ ህዝብ ስላላቸው አይደለም እነርሱ አሁን ካሉበት ደረጃ የደረሱት።

## ክፍል 2. " ኢትዮጵያን የሚያዉኩ ጉዳዮች"

ይሄ ክፍል አገራችንን እንደነቀርሳ ቆፍድዶ ይዞ ሕዝባችንን የአልጋ ቁራኛ አድርጎ ያስቀረዉን የአምባገነን ሥርዓት ያትታል። በዘዉዱ አገዛዝ ዘመን ድህነት፣ በሽታና ድንቁርና እንዲጠፉ ስለተደረጉት ትግሎችና ደርግም ተሹለክልኮ ስልጣኑን ከሕዝብ ሲነጥቅ ስለተደረገዉ ቀጣይ ሕዝባዊ ትግል ባጭሩ ይጠቅሳል።

## 2.1 የህወሃት/ኢህአደግ አምባገነናዊ ሥርዓትን በተመለከተ፤

ዋናዉ የመጽሐፉ ትኩረት ግን የአሁኑ የህወሃት/ኢህአደግ  ጎማዊና አምባገነናዊ ሥርዓት ባስከተላቸዉ አሰቃቂ ችግሮች ላይ ነዉ። እነዚህንም እንደሚከተለዉ ይዘረዝራል፤

- "በስም ዲሞክራሲን እያቋቋምኩ ነዉ እያለ እየለፈፈ በተግባር ግን አጼ በጉልበቱነቱን አስፍኖ ... ሙሉ የምዝበራ፣ የዝርፊያ፣ የህዝብ መብቶች ረገጣ፣ የድህነትና የርሃብ መስፋፋት እንዲሰፍኑ" ስለማድረጉ፤
- የዉጪ ኃያላን መንግሥታትን የዲሞክራሲ ወዳጅ ነኝ ብሎ ለማሳመን ሲያደርገዉ የቆየዉ ማጭበርበር፤
- የምርጫ ሳጥኖችን በህሰተኛ ወረቀቶች እያስሞላ ወይም እያስገለበጠ ያለሀፍረት አሸነፍኩ ለማለት ስለመራወጡ፤
- ይባስ ብሎ በህዝብ ድምጽ የወደቁትን ሚኒስትሮች መልሶ ስለማስገባቱ፤
- ተቃዋሚ ወገኖችን ማስፈራራትና ማፈን፤
- የግል ጋዜጦችን ክትትል ሥር ማዋልና ከአዲስ አበባ  እንዳያልፉ ማገድ፤
- በአዲስ አበባ ላይ ግን ዓለም ዐቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች በግድ እንዲመለከቱ በመገደዱ ምርጫዉ በክፍለ ሀገራት እንደተደረገዉ ሊጭበረበር ባለመቻሉ ምክንያት ሚኒስቴሮች ጭምር ስለመታጨዳቸዉና ካቢኔዉ እንዳለ ካንገቱ ላይ በህዝብ ተቆርጦ ስለመዉደቁ፤
- ቃል የገባዉን የነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሥነ ሥርዓት ማከናወን ተስኖት የድምፅ ሳጥን ማስገልበጥና ቁጥር ማምታታት ዉስጥ ሰሲነከር ከግምት በታች የዉዳቂ ዉዳቂ መሆኑን ስለማስመስከሩ፤
- ወዲያዉ የድምፅ ማጭበርበር ክስ የሰነዘሩበትን ተቃዋሚ ድርጅቶች ዐመፅ ሊያስነሱ ነዉ በማለት ወህኒ ቤት ስለማጎሩ፤
- ወዘተ፤

በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ መልሶቹ ግልፅ ቢሆኑም ለትዝብት ያክል አንዳንድ ነጥቦችን መልሶ ማንሳት ያሻል፤

- ገና ከምርጫዉ በፊት የነቃዉ ህዝባችን የሰጠዉ ዉሣኔ ለምን ተናቀ?
- እንደእነ አና ጎመዝ (ከአዎሮፓ ህብረት የተላኩ የምርጫዉ ታዛቢ የነበሩ) የመሳሰሉ ሃቀኞች ታዛቢዎች ጭምር የተሰጡትን ግምገማዎች  መርገጥና ዉሸትን መደጋገም ራስን ለማታለል ካልሆነ በስተቀር ለምን አስፈለገ?
- ገና ለገና ለኃያላን መንግሥታት ቡችላ በመሆን ተከታታይ ጥፋቶችን መፈጸም እስከምን ሊያደርስ ነዉ?

"በ21ኛዉ መቶ ኢትዮጵያ ዋናዉ ጥያቄ ሁሉንም የፖሊቲካ ኃይሎች በእኩልነት፣ በነፃነትና በፍትሕ ባንዲራ ሥር አሰባስቦ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ነዉ። ሁለተኛዉ ታላቅ ጥያቄ ባብዛኛዉና በመጀመሪያ ድህነትን፣ ርሃብን፣ በሽታንና የአካባቢ ተፈጥሩ መሚጠጥን ለመቋቋም ሁሉንም የኢኮኖሚ ሀብቶች ማንቀሳቀስና" ሥራአጥ ወጣቶችን መንከባከብ እንደነበረባቸዉ ደህና አድርጎ ያትታል።

ባለመሆኑም ባለሥልጣናትና አባሪዎቻቸዉ የህዝብን ኃብት ዘርፈዉ ሲናጥጡ ህዝባችን የሚላስ የሚቀመስ ነገር አጥቷል። ይሄን ችግር ሲያብራራ መጽሐፉ እንዲህ ይላል፤ "አነስተኛ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እየታፈኑና ለተወሰኑ በተለይ በፖሊቲካ መሣሪያነት ለሚታሰቡ ክፍሎች እየተከለሉ በገጠርና በከተማ ከዩኖቬርሰሲቲዎች የሚተፋዉ የተማረ ኃይል ቀርቶ አሥረኛ ክፍል ላይ ያልተሳካለት ወጣት አገሩን እየለቀቀ ወደሙጭ እየኮበለለ

ነዉ። ታሞ ሃኪም ቤት የገባ ሰዉ የመዳን ዕድሉ አስተማማኝ ከማይሆንበት ወደማይድንበት ጊዜ እየወረደ ነዉ" ይላል። ዛሬ ባንዲት ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ ብቻ ከመቶ ሺህ በላይ የሆኑት ወጥቶች ለዕንግልትና መከራ የተዳረጉት አገራችን ድሂ በመሆንዋ ሳይሆን ያገሪቷ ንብረት ርህራሄ በሌላቸዉ ጥቂቶች እጅ በመዉደቁ ምክኒያት እንደሆነ ይብራራል።

በትምህርት ቤቶችና በዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጠዉ የትምህርት ጥራት እጅግ እያሽቆለቆለ መሄዱን እንደሚከተለዉ ያሳያል። "የትምህርቱ ሥርዓት ለነጋዴዉና ለቢሮዉ ባለሥልጣናት የግል ትርፍ ማሳደጃ እንዲሆናቸዉ ከተከፋፈተ ጀምሮ አገሪቱ የምስክር ወረቀት ማምረቻ ድርጅቶች የሚርመሰመሱባት ሆናለች፤ በቦታ ጥበት የትምህርት መሣሪያዎች አለመዳረስ፤ የመምህራን ደመወዝና ጥራት መዉደቅና በተማሪዎች መሃል ከትምህርት በኋላ ሕይወታቸዉ የማይለወጥ የመሆኑ እምነት እየተስፋፋ መማርን እየሸሹ የሥራአጡን ቁጥር ማሳደጋቸዉ የተሟላ መፍትሄ እንዲሰጣቸዉ ያስፈልጋል" በማለት ያሳስባል። ችግሩም በርግጥ እጅግ አሳሳቢ ነዉ። ጥራት ያለዉ ትምህርት ለባለሥልጣናትና ለነርሱ ነጋዴዎች ልጆች ብቻ ከሆነ የሰፊዉ ህዝብ ልጆችና የአገሪትዋ ፅጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመትና ለላስተካከል መሞከር የሁሉም ንፁሕ ዜጋ ኃላፊነት እንደሆነ ጨምሬ ላሳስብ እወዳለሁ።

## 2.2 ተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶችን በተመለከተ፤

በ1997ቱ ምርጫ ዉስጥ የተሳተፉትን ተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶች በተመለከተ "... ሳያዉቁትና ሳይጠብቁት ገንፍሎ የተነሳዉን ህዝብ እንኳን በቅጡ ከጎናቸዉ ለማሰለፍ አልተቻላቸዉም " ይላል መጽሐፉ። እንደ ዕዉነቱ ከሆነ ህዝቡን ከጎናቸዉ ማሰለፉ ቀርቶ ከነርሱ በላይ ነቅቶ የነፃ ምርጫ ሥነ ሥርዓት በሌለበት ምርጫዉ ዉስጥ መሳተፉ ቀርቶ ሃሳቡም እንዳይኖራችሁ እያለ በነቂስ ወጥቶ ግልፅ ሃሳቡን የሰነዘረዉንና መብቱን ለማስጠበቅ ቆርጦ የተነሳዉን ህዝብ እንኳን ሊከተሉ አልቻሉም።

ከ1997ቱ ምርጫ በፊት በለንደን አንድ ትልቅ ህዝባዊ ስብሰባ ተጠርቶ ነበር። በዚያ ስብሰባ ላይ የተገኙት ሁለት ተናጋሪዎች ከኢትዮጵያ የመጡ ሲሆን አንደኛዉ ከህብረት ሌላኛዉ ከቅንጅት ነበር። በምርጫዉ ውስጥ መሳተፉን በተመለከተ እንዳንድ ጥያቄዎች ቀርበዉላቸዉ ነበር። የህብረቱ አባል ያለዉን ጭቆናና ግፍ ካብራሩ በኋላ "የተራበ ህዝብ መሪዉን ይበላል" ብለዉ ህዝቡን ትንሽ አስጨብጭበዉ ነበር። የምርጫ ቦርዱ ሰብሳቢ የመንግሥት ባለሥልጣን በሆነበትና ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በማይኖርበት እንዴት ትሳተፋላችሁ? ተብለዉ ለተጠየቁት ጥያቄ የቅንጅቱ አባል ሲመልሱ የሚከተለዉን እጅግ አሳዛኝ ነገር ተናገሩ፤ ምርጫዉ ውስጥ እንሳተፋለን፤ ምርጫዉ ቢጭበረበር ከማል በድሪን (የምርጫዉ ቦርድ ሰብሳቢና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዴንት መሆናቸዉ ነዉ) ፍርድ ቤት እንወስደዋለን፤ ፍርድ ቤቱ ነፃ ነዉ ብለዉ ቁጭ አሉ። እንደተባለዉም አልቀረ፤ በአገር ዉስጥ የሚንቀሳቀሱት ሁለቱ የህብረት ፓርቲዎችና መላዉ የቅንጅት አባላት በምርጫዉ ተሳተፉ። ከዚያ በኋላ የደረሰዉ አሳፋሪ ዉድቀት ህዝባችን ቀድሞ የተናገረዉ ነገር ነዉ።

የህብረት መላላቱን ችግር በተመለከተ መጽሐፉ እንዲህ ይላል፤ "በፖሊቲካ ቡድኖች መሃል ሁሉንም አስወግዶ ወደ ሥልጣን ለመዉጣት የሚደረገዉ እንደነቀርሳ የተራባዉን ምኞት እንዴት መዋጋት ይቻላል"? ብሎ ይጠይቅና መልሱን እንደሚከተለዉ ይጠቁማል፤ "መልሱ ቀላል ነዉ። ነጠላ ጥያቄዎችን ይዘዉ የሚፈሯጡትን ወይም የየራሳቸዉን የአይጥ ጉድጓድ ቆፍረዉ መጠለያ የሚያበጁትንና በር ሲከፈትላቸዉ ፈትለክ ብለዉ ወደ ሥልጣን ለመዉጣት የሚያቃዠቸዉን መደገፍ ይቁም!! **ተደራራቢ ዓላማዎችን የሚያራግቡትንና ከሌሎች ጋር**

**አብረዉ ሠርተዉ ሰፊና የበለጠ ተግባራዊነት ያለዉ የተባበረ እንቅስቃሴ ሊመሠርቱ ዝግጁና ፈቃደኛ መሆናቸዉን የሚያዉጁትን ማበረታታት፤ መደገፍ፤ ማቀፍ!!! ከ1997 አጠቃላይ ምርጫ በተገኘዉ ልምድ ህወሃት/ኢህዴግን ሥልጣን ለማላቀቅ የሚቻለዉ ሰፋ ያለና በተሻለ አኳኋን የተደራጀ ፖሊቲካ ኃይሎች ጥምረት ሲኖር መሆኑን አሳይቷል“።**

በርግጥ ተገቢ አባባል ነዉ። የ1997 ምርጫ ዝግጅት ጉድፈት ብዙ ዕድሎችን አስመልጦናል። ባንድ በኩል በህብረት ሥር ተስማምተዉ ተማምለዉ የተነሱት 15 የተቃዋሚ ድርጅቶች በቃል ኪዳናቸዉ ፀንተዉ ቢቆሙ ኖሮ የ1997ቱ ምርጫ እንደዚያ ርካሽ፤ ዉዳቂና መሳቂያ ሆኖ ባልቀረ ነበር፤ ህወሃት/ኢህአዴግም የህዝቡን ድምፅ አክብሮ ሥልጣኑን በሰላም ቢያስረክብ ኖሮ ታላቅ ተግባረ በመፈፀሙ ላለፉት ጥፋቶቹ ይቅርታ ተደርጎለት በታሪክ ፊት ተከብሮ ተመስግኖ ሊኖር ይችል ነበር። ዳሩ ግን ህዝብም አምላክም የሚወደዉን ሥራ እነደመፈጸም የሴይጣንን ጎዳና መከተሉ ህዝባችንን ሰብስቦ ርሃብ፤ ችጋርና ብትብጥ ዉስጥ ሲከት ጊዜያዊ አሳፋሪ ጥቅም እንደሆነ እንጂ ዘለቄታ ያለዉን ደስታ ሊያገኝ የሚችል ወገን ከቶ አይኖርም፤ “ዎበጊዜ ለኹሉ“። በእነደርግ፤ በግብፁ ሆስኒ ሙባረክ፤በኢራቁ ሳዳም ሁሴን፤ ወዘተ ላይ በመጨረሻ ቀኑ ሲደርስ የሚያስከትለዉን ቅሌትና ዉርደት ብቻ መገንዘቡ ይበቃል። ለሁሉም ጊዜ አለዉ፤ እንኳንስ የግብዝ አምባገነኖች ዘመን ቀርቶ ዓለም ራሷ ለ8ኛዉ ሺህ መቃረብዋን የሚያረጋግጡ ግልፀ ሆኑ ምልክቶች እየታዩ ናቸዉ።

## 2.3 የዉጪ ኃያላን መነግሥታትን ጣልቃ ገብነት በተመለከተ፤

*“የዉጪ ኃያላን መነግሥታትን ፍላጎት በተመለከተ መጽሓፉ እንደህ፡ይላል፤ አሜሪካኖችና አባሪዎቻቸዉ ዉስጧ የተዳከመ፤ በዘርና በሃይማኖት ዉጥረት ተሳስራ የምተኖር አገር ላይ ቁትጥራቸወን ሲያጠብቁ በሙሉ ዕዉቀት ነዉ። ብትዳከምም በራስዋ መተማመን እየቀነሰች ከነርሱ ሥር በቋሚ ጥገኝነት ብትሸጎጥም ባካባቢዉ ፖሊቲካ የሚያቅዱትን ትልም እንዳሻቸዉ ለማስፈጸም እንደምትረዳቸዉ ያዉቃሉ“። በማለት እቅጩን አስቀምጠዋል። በርግጥ ነዉ፤ በመቅደላ፤ በአድዋ፤ በማይጨዉ፤ ወዘተ ሞከሩን፤ ሊያጠፉንም ሆነ ጥገኛ ሊያደርጉንም እስካሁን አልቻሉም ነበር፤ ዕድሜ ላገር ወዳድ አርበኞች አባቶቻችንና አያቶቻችን ህብረትና ደም። የኃያላን መነግሥታት ጠባይ ደካሞች አገሮችን መዉረር፤ በቡችላ መሪዎች አማካኝነት ህዝቡን ከፋፍሎ መግዛት፤ መቆጣጠርና ሃብቶችን መዝረፍ ልማዳቸዉ ነዉ። የባርነት ዘመን፤ የቅኝ አገዛዝና የእጅአዙር ቁጥጥር በታዳጊ አገሮች ላይ ምን ያህል ችግሮች እንዳስከተለ ግልፅ ነዉ። አትርራን ሲያስገነጥሉ ለኤርትራ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን ኢትዮጵያን ለማዳከም እንደሆነ በጌአድ የታዩ ሃቅ ነዉ። እጅግ በጣም የሚያሳዝነዉ ግን ትናንት የአሜሪካ እምፔሪያሊዚም ይዉደም፤ ጭቁን ህዝብ ያሸንፋል እያሉ ሲጮሁ የነበሩት የራሴ ትዉልዶች ዛሬ ዐይናቸዉን በጨዉ አጥበዉ ለራሳቸዉ ሥልጣንና ዝርፊያ ዉድ አገራችንን ለባዕዳን መሸጣቸዉና ጥፋትዋን በማመቻቸት ላይ መገኘታቸዉ እግዚኦ መሃረነ ክርስቶስ፤ ኤሎሄ ኤሎሄ፤ አላሁ አክበር ያሰኛል።*

## 2.4 የግለሰቦችና ቡድኖች ሚና፤

*የመጽሐፉ ዋና ዓላማ በተለያዩ አንገብጋቢ ጉዳኦች ዙሪያ ጠለቅ ያሉ ምርምሮችና ዉይይቶች እንዲደረጉ ለመጋበዝ ነወ እንጂ ለሁሉም ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንዳልሆነ ደራሲዉ ገልጸዉታል። ስለዚህ ማንኛዉም ሰላምና ዕድገት ፈላጊ ዜጋ አገራችንን ከባሰዉ ዉድቀት ለማዳን የሚቻለዉን ሁሉ አስተዋጽኦ እንዲአደርግ ጨምሬ ልማፀን እወዳለሁ።*

*ሀ)* *አገራችን ያለችበትን መከራና ወዴት እያመራች እንዳለች ጠንቅቆ ማወቅ፤*

ለ) በራሳችን ላይ ባህላዊ ዐብዮት ማካኼድ፣ ልባችንን ንፁሕ ማድረግ፣ ከሁሉም በላይ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዳይርቀን መሞከር፣ መደማመጥ፣ መከባበር፣ ሂስና ግለሂስ መቀበል (የዲሞክራሲ ፕሪነሲፕል ማዳበር)፣ ስለአሁኑና ስለመጪዉ ትዉልድ ደህንነት ማሰብ፣

ሐ) ለኩርማን መሬትና ለጥቃቅን ጥቅሞች አገራችንን አለመሸጥና ከሚሸጧትም ጋር አለማበር፣ 'ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ' የሚለዉን ሴይጣናዊ መርሆ መጣልና ከስግብግብነትና ከርካሽ ራስ ወዳድነት መታቀብ፣ 'ዎአዳም አንተ መሬት ዎትገብር ዉስተ መሬት'!!!

መ) የተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶች የዲሞክራሲ ጥያቄ ሁሉንም እኩል የሚመለከት ከሆነ በዚያ ዙሪያ በቅርብ መተባበር፣ የዲሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ ህዝበ ዉሳኔ ስለሆነ ገና ህዝብ ፊት ሳኢደረሰ ከወዲሁ መናቆሩና መጠላለፉ ኢዲሞክራሲያዊ መሆኑን ማወቅና መገደብ፣ ለምሣሌ በ2003 ዓ/ም 15 ተቃዋሚ ድርጅቶች ተስማምተዉ ህብረት የፈጠሩበትን ሠነድ ማስታወስና ማንሰራራት፣

ሠ) ተመሳሳይ አገሮች እንዴት ወደዕድገት ደረጃ እንደደረሱ መመርመርና ጥናታዊ ሠነዶች ማቅረብ፣

ረ) ዉጭ አገር በተሻለ ኑሮ የሚኖሩ ወገኖች፣ የግል ባለሃብቶች (ባለሆቴሎች፣ ዘፋኞች፣ ስፖርተኞች፣ ወዘተ) ከጎዳና ተዳዳሪ እጓለማዉታን መሃከል አንዳንድ ልጅ ቢደግፉ ተልቅ አስተዋጽኦ ነዉ፣ ዛሬ የሆቴል ትራፊ እንኳን መሸጡን ለሚሰማ ጆሮ ምንኛ እንደሚቀፍ መናገሩ ራሱ ያሳፍረኛል። ወጣት እንደዚያ መንገድ ላይ ሲራብ ትራፊ መሸጡ ዬት እንደሚያደርስ ከቶ አይገባኝም። የ"ዓሣ ግማቱ ካናቱ" እንደተባለዉ መሆኑ መሰለኝ የላይኛዉን ጥፋት መከተል። ድሮ በደህናዉ ዘመን "ለኔ ቢጤዎች" ይባል ነበር።

ሰ) ማንኛዉም የሃይማኖት ተቋም ሲደፈርና ሲጎዳ ሁሉም ዜጋ ባንድ ላይ መቆምና መከላከል፣

ሸ) ካገር ዉጪ ወገኖቻችን ሲደፈሩ አሁን በማሳየት ላይ ያለንበትን ትብብር ማጠናከር፣

ቀ) በአገራችን ዲሞክራሲና ሰላም ከሰፈነ ሁሉም ዜጋ በደስታ መኖር መቻሉን መገንዘብና አገር በማዳኑ የጋራ ትግል ላይ መረባረብ፣

በ) የሙያ ማህበራትን በያገሩ ማቋቋምና አለም አቀፋዊ ትብብር መፍጠር፣ በነዚህም ሥር የምንመለከታቸዉ ጉዳዮች የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል፣

- የመሬት ይዞታ የፖሊሲ ጽንሰ አሳቦች መንደፍና ማወያየት፣
- የግብርናና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ዘዴዎችን መመርመርና መንደፍ፣ ዘለቄታ ያለዉ የአገር ኢኮኖሚ እድገት ሊመጣ የሚችልባቸዉን አቅጣጫዎች መሰንዘር፣
- የአፈር፣ የዉሃ/ የተፈጥሮ ኃብትና የአካባቢ አየር ጥበቃ ዘዴዎችና ፖሊሲዎች መመርመርና መንደፍ፣
- የትምህርት ፖሊሲወዎችን መመርመርና መንደፍ፣
- የጤና ፖሊሲዎችን መመርመርና መንደፍ፣
- ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ሊታበረክት የምትችላቸዉን ቁልፍ አስተዋጽኦዎች በግልጽ ማስቀመጥና ከዉጪዉ ዓለም ጋር መፍጠር የሚገቡንን ግንኙነቶች መመርመር፣ዲሞክራሲ፣ ሰላምና ዕርጋታ ከሌለ ዓለም ሁለ ሊኖወጥና ዘለቀቄታ ዕድገት ሊኖር እንደማይችል ማወቅና ማሳሰብ፣
- የተማረዉን ክፍል ማግለል አገራችንን ለባርነት ማመቻቸት እንጂ ዘለቄታ የሚኖረዉን ዕድገት ማምጣት ከቶ እንደማይቻል ደጋግሞ ማስገንዘብ
- የሕግ ባለሙያዎች ተደራጅተዉ የህዝብ እልቂትና የአገር ንበረት ዝርፊያ የፈጸሙትንና እንደዚሁም ሕፃናትንና ዜጎችን ለባዕዳን ለባርነት የሚሸጡትን ወንጀለኞች ወደ ዓለም አቀፍ የፍትሕ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡበትን መንገዶችና ሁኔታዎች ማጥናትና ማመቻቸት
- ወዘተ፣

አማርኛችንን በተመለከተ ደራሲዉ ብዙ ጠቃሚ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል።አማርኛ ከሁሉም የበለጠ፤ እጅግ የዳበረና የሰለጠነ ቋንቋ ነዉ። ቋንቋዉን በመጠቀም ማንኛዉንም በዓለም ላይ ያሉትን ድምፆች መጥራት ይቻላል። ፊደሎቻችንን በመጠቀም ማንኛዉንም በዓለም የሚሰማ ቃል መፃፍ እንችላለን። ታዲያ ለብዙ ሽሲህ ዓመታት የዳበረዉን ቅርሳችን የምንንቀዉ ለምንድን ነዉ ብለዉ መጠየቃቸዉ እጅግ ተገቢ ነዉ። በርግጥም አመሰግናለሁ ለማለት ቴንክዩ፤ እማማ፤ አባባ፤ እማዬ፤ አባብዬ በሚሉት አንጀት በሚበሉ ቃላት ምትክ ማዘር፤ ፋዘር እያሉ መበሻቀጥ ምን ለመሆን እንደሆነ ጨርሶ አይገባኝም። አማርኛ ጠፍቷቸዉ እንዳይባል ባገር ዉስጥ ናቸዉ። እንግሊዘኛዉ ቀልሏቸዉ እንዳይባል ምን ያህል ችግር እንዳለባቸዉ እነርሱም አካባቢያቸዉም ጠንቅቆ የሚያዉቀዉ ነዉ። ባንታደል ሆኖ እንጂ እንኳንስ ብሄራዊ ቋንቋችንና የቤተክርስቲያናችንና የሥልጣኔያችን መሠረት የሆነዉን ግዕዝ ጭምር መልሰን ብናንሰራራ በተገባ ነበር።

## 2.5 መጽሐፉ የዳሰሳቸዉ ሌሎች ጉዳዮች

መጽሐፉ በተጨማሪም በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦችን ሰንዝሯል፤

- የሃሳብ ነፃነትና መገለጫዎች፤ መገናኛ ብዙሃን በኢንተርኔት ዘመን
- የጥበብ ሽግግር ጉዳይ
- የቤት አሠራር ጥበብ
- ዲያስፖራና የጥበብ ሽግግር
- የኢቲዮጵያ ሥነጽሑፍ ይዞታ
- የርዳታ/ብድር ኢኮኖማና ጣጣዎች
- ፊልሞች በኢትዮጵያ
- ኢትዮጵያና ምሥራቅ አፍሪቃ

## 2.6 የመጻሕፍት ግምገማ

ደራሲዉ በተጨማሪም የሑለት መጻሕፍት አጫጭር ግምገማዎች አቅርበዋል።

አንደኛዉ በእነ አንድርዜይ ባርትኒስኪ ተጽፎ በአለማየሁ አበበ የተተረጎመ የኢትዮጵያ ታሪክ ነዉ። መጽሐፉ የኢትዮጵያን ታሪክ ከአክሱም ጀምሮ እስከዐፄ ምኒልክ አገዛዝ  ድረስ የሚያትት ነዉ። ከመጽሐፉ አደራረስ የሚገኘዉ አንዱ ትልቅ ቁምነገር ከሩቅ ሆኖ  በጥራዝ ነቀስ ሳይሆን አገር በቀል የሆኑትን መረጃወዎች በማሰባሰብ ሁሉንም ማህበራዊ፤ ገጽታዎች (የባህል፤ የእምነት፤ የምጣኔ ሀብት፤ የህዝብ እንቅስቃሴ፤ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች፤ ንግድና ሥነጥበብ) መመርመር እንደሚገባ ነዉ።

ሁለተኛዉ ግምገማ ኣና ካረኒን በተባለዉ የሊዮ ቶልስቶይ መጽሐፍ ላይ ነዉ። የ መጽሐፍ የተዘጋጀዉ ሩሲያ በመካከለኛዉ ዘመን በጭለማ ዉስጥ በነበረችበት ጊዜ የነበሩትን ችግሮች ለማስወገድ በቂ ግንዛቤ ባልነበረበት ወቅት ነዉ።በዚያ ወቅት ነበር ሊዮ ቶልስቶይ “ለሪሲያ ህብረተሰብ ማህበራዊ ታሪክ ትልቅ ሃዉልት አቁሞ ያለፈዉ“።

ኢትኦጵያም ዛሬ ዲሞክራሲን ልትገነባ ባለመቻልዋ ጭለማ ዉስጥ ብትገኝም የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከዚያን ዘመኑ ሩሲያ በጣም ይለያል፤ ዲሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችሉ ሁሉም ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሳለ በአምባገነን መንግሥታት አፈናና በተቃዋሚ ድርጅቶች መሃከል ህብረት መላላት ምክንያት ብርሃን መፈንጠቅ ስንችል በጭለማ ዉስጥ እንድንሰቃይ የተዳረግነዉ።

ያድህነነ እመዓቱ ይሰዉረነ!!!